የትግራይ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የአይቲ ዕቃዎች (IT Equipment)፣ ኤሌክትሪክ ጀነሬተርና አነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች፣ የእንሰሳት ሕክምና መገልገያ ዕቃዎች፣ የማንጎና የአቮካዶ ፍሬ በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ሶኒ ታሕሳስ 1, 2011 (ከ 8 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ታሕሳስ 30, 2011 3:30 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:ኣልተገለፀም
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ: 100.00
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ታሕሳስ 30, 2011 4:00 ጥዋት
- ምድብ: ፍዮሪን ሆልቲካልቸር/ ኮምፒተርን ተዛመድቲ / ናይ ኮምፒተር ተዛመድቲ አቁሑትን/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቁሑትን ግልጋሎትን/ ናይ መድሓኒት ምህርቲ/

የጨረታ ማስታወቂያ

ጨረታ ቁጥር TG/AGP-CU

10/2011

የትግራይ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም (AGP-II) በተገኘ በጀት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ማለትም:-

- ሎት 1. የአይቲ ዕቃዎች (IT Equipments)
- ሎት 2. ኤሌክትሪክ ጀነሬተርና አነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች
- ሎት 3. የእንሰሳት ሕክምና መገልገያ ዕቃዎች
- ሎት 4. የማንጎና የአቮካዶ ፍሬ

በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

በመሆኑምበጨረታውላይለመሳተፍ የምትፈልጉ በዘርፉ ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላችሁ አቅራቢ ድርጅቶች በጨረታው እንድትሳተፉ እ የጋበዝን የተዘጋጀው የጨረታ ዶክመንት ለእያንዳንዱ የማይመለስ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብ/ በመክፈል ከታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ከቢሮአችን የዕቃ ግዢ ንዑስ ሥራ ሂደት በሥራ ሰዓት እየመጣችሁ መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እየገለፅን በጨረታዉ ላይ ለመሳተፍ ቀጥለዉ የተዘረዘሩትን ማሟላት ይጠበቅባችኋል።

- የዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ የአቅራቢዎች ምዝገባ ሠርተፊኬት፣የቫት ሰርተፈኬት፣ ያለፈዉ ወር ቫት ሪፖርት የተደረገበት ማስረጃ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (ቲን) ማስረጃ ፎቶ ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።
- ተጫራቾች የጨረታ መመሪያውን በጥንቃቄ አይተው መወዳደርአለባቸው።
- የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ በጨረታ ዶክመንቱ ላይ የተገለፀዉን መጠን በቢሯችን ስም በሲፒኦ አሠርተዉ ጨረታዉ ከመከፈቱ በፊት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ቢሮአችን በጨረታ ከቀረበው የዕቃዎች ብዛት እስከ 15% ለመቀነስ ወይም ለመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነዉ።
- ጨረታው ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ በ3፡30 ሰዓት ተዘግቶ በዚያዉ ዕለት በ4:00 ሰዓት ላይ መገኘት የሚፈልጉ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቢሮአችን የዕቃ ግዥ ንኡስ ሥራ ሂደት ይከፈታል።
- ቢሮአችን የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥሮች 0344-403663፣ 0344-404723 ወይም በፋክስ ቁጥር 0344-409971 መጠየቅ ይቻላል።

የትግራይ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ